# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 334 መስከረም 24


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በፀጥታ ጉዳይም ቢሆን አሜሪካ የያዘችው አቋም በረዥም ጊዜ የኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን የአሜሪካን ጥቅም የሚጎዳ ነው ብሎ ያምናል። ኢትዮጵያ ለአሜሪካ ከወታደር ምንጭነት በላይ የምታገለግል አገር ናት። ኢትዮጵያ ውስጥ ከራሱ ሕዝብ ጋር የታረቀ መንግሥት መኖር ለቀጠናው ሰላም እና ብልጽግና ወሳኝ ከመሆኑም በላይ የቀጠናው ሰላምና ብልጽግና የአሜሪካም ስትራቴጂያዊ ጥቅም ነው ብለን እናምናለን። የአጫጭር ጊዜ ጊዜዓዊ ጥቅሞችን ብቻ በመመልከት አምባገነኖችን መደገፍ አሜሪካን ምን ያህል ውድ ዋጋ እያስከፈላት እንደሆነ በዓይኖቻችን እያየነው ያለ ሀቅ ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የአውሮፓ ህብረት የአንዳርጋቸዉ ጽጌን መታሰር አወገዘ- የነጻነት ታጋዩ እንዲፈቱ ጠየቀ

የግንቦት 7 የፍትህ፡ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ዋና ፀሃፊ የሆኑት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ አለማቀፍ ህግን በጣሰ ውንብድና ከየመን ሰንአ አየር መንገድ ታፍነው ለጉጅሌው ወያኔ ተላልፈው ከተሰጡ ወራቶች ተቆጥረዋል። አለማቀፍ ህግን በጣሰ አካሄድ ለፋሽስቶች ተላልፈው የተሰጡት የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የተለያዩ አለማቀፍ ተቋማትንና የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችን በእጅጉ ያሳሰበ መሆኑ በተለያየ ጊዜ በድርጅቶቹ መገለጹ የሚታወስ ሲሆን ከሰሞኑ በጉዳዩ ዙሪያ የመከረው የአውሮፓ ህብረት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ህገ ወጡን ድርጊት በማውገዝ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ እንዲፈቱ ጠይቋል። ኮሚሽኑ አቶ አንዳርጋቸው የፖለቲካ እስረኛ መሆኑን በማመልከት በኢትዮጵያ ለዲሞክራሲ፣ ነጻነት፣ መልካም አስተዳደር እና ሰብአዊ መብት መከበር የሚታገል አርበኛ እንጂ ሽብርተኛ አይደለም በማለት ባስቸኳይ ተለቆ ወደ እንግሊዝ እንዲመለስ አሳስበዋል።

በውይይቱ ላይ የተገኙት የአውሮፓ ህብረት ኮሚሽን አባል የሆኑት የተከበሩ ሚስስ አና ጎሜዝ ፋሽስቱ ወያኔ በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ላይ የወሰደውን ህገወጥ የውንብድና ተግባር ያወገዙ ሲሆን አገዛዙ በኢትዮጵያ በርካታ ንጹሃን ዜጎችን አስሮ እያሰቃየ እንደሚገኝ በመግለጽ አለማቀፍ መንግስታትና የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች በአገዛዙ ላይ ጠንከር ያለ እርምጃ እንዲወስዱ ጠይቀዋል። በአገዛዙ የፈጠራ ክስ በህገወጥ መንገድ የታሰሩት ብሎገሮቹ የዞን 9 አባላት፤ ጋዜጠኞችና የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና አባላትም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲለቀቁ ግፊት ይደረግ ዘንድ ኮሚሽኑን አሳስበዋል።

የአውሮፓ ህብረት ኮሚሽኑ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ በአቶ አንዳርጋቸው ጉዳይ ዙሪያና በኢትዮጵያን ያለውን የሰብአዊ መብት አያያዝን በተመለከተ በጥልቀት ለመምከር ቀጠሮ ማሳለፉ የታወቀ ሲሆን ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወያኔ የመንግስት ሰራተኞችን አስገድዶ ማሰልጠን ጀመረ

የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ላለፉት ሳምንታት ለተለያዩ አካላት ሲሰጣቸው የነበረው የፖለቲካ ስልጠናዎች ያለ ምንም ውጤት በተቃውሞዎች እየተናጡ ተካሄደው መጠናቀቃቸውን እየተከታተልን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን በደረሰበት የህዝብ መራር ተቃውሞ ከፍተኛ ውጅንብር ውስጥ የሚገኘው አገዛዙ አሁንም ለቀጣዩቹ አስር ቀናቶች በፈረቃ ለመንግስት ሰራተኞች አስገዳጁን የገለማ የዘር ፖለቲካ ስልጠናውን መስጠት መጀመሩን ለማወቅ ተችሏል። እንደ ከዚ ቀደም ስብሰባዎች ሁሉ አገዛዙ በመንግስት ሰራተኞች ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞ ሊገጥመው እንደሚችል ተነግሯል።

የህዝቡን ስነ ልቦና በመስለብ አፍኖ እና ቀጥቅጦ ለመግዛት እንዲያመቸው አስገዳጅ የፖለቲካ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት ለተለያዩ አካላት እየሰጠ የሚገኘው አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በተለይ በየስልጠናዎቹ  ላይ ከህዝቡ ያገኛቸው የተቃውሞ ምላሾች እጅግ አስደንጋጭ እንደሆኑበት ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በተለይ በመጭዎቹ ጥቂት ጊዜያት ውስጥ የኢትዮጵያ ህዝብ በተቀናጀ ሁኔታ ለበቀል ሊነሳብኝ ይችላል በሚል ከፍተኛ ስጋት ውስጥ ወድቆ እንደሚገኝ ከውስጥ ምንጬችን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

በተያያዘ ዜና ፋሽስቱ ወያኔ ለአስገዳጁ የፖለቲካ ስልጠና ማስኬጃ በሚል ከፍተኛ የአገር ሃብት ማባከኑ የታወቀ ሲሆን በተለይ በየ ስልጠናዎቹ በአስተባባሪነት የተመደቡት የአገዛዙ ቅጥረኛ ካድዎችም በከፍተኛ ሙስናና ምዝበራ ላይ መሰማራታቸውን የውስጥ ምንጬችን አመልክቷል።

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## ወያኔ የክልሉ ፕሬዚዳንት አድርጎ የሾመዉ አብዲ ሙሃመድ የሶማሌን ክልሉ አስገነጥላለሁ ሲል ዛቻ ሰነዘረ

በጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ የሶማሌ ክልልን እንዲመራ የተሾመው አሻንጉሊቱ አብዲ ሙሃመድ አገዛዙ እሱን ከስልጣን ለማውረድ አንዳች ሙከራ ቢያደርግ ክልሉን አስገነጥላለሁ ሲል መዛቱን ተከትሎ በክልሉ ውጥረት መንገሱን ለማወቅ ተችሏል። ክልሉን በተመለከተ የወያኔን ቱባ ሹም አብዲ ሙሃመድን ለማነጋገር አሻንጉሊቱ ሃ/ማርያም ደሳለኝ ጥሪ አቅርቦ የነበረው ቢሆንም ለመሄድና ለማነጋገር ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱ ታውቋል። ህወሃት እንጂ አሻንጉሊቱ ሃ/ማርያም እኔን ፈጽሞ ሊያዘኝም ሆነ ክልሉን በተመለከተ ሊያነጋግረኝ አይችልም ሲል መናገሩ ተመልክቷል። ለአሻንጉሊቱ ሃ/ማርያም ደሳለኝ ከፍተኛ ንቀት እንዳለው በጉጅሌዎቹ ቱባ ሹማምንቶች ዘንድ ጭምር በሚገባ የሚነገርለት የክልሉ አስተዳዳሪ በተለይ ሃይለማርያም ማንንም የማዘዝ ብቃት እንደሌለው በድፍረት ሲናገር በተደጋጋሚ እንደሚደመጥ የውስጥ ምንጬችን ያደረሰን መረጃ ያሳያል። ከአሻንጉሊቱ ሃይለማርያም የቀረበለትን ጥሪ በንቀት መግፋቱን ተከትሎ እሱን ለማነጋገር በሚል ወደ ክልሉ የተላከውንና በሽፈራው ጃርሶ የተመራውን የልዑካን ቡድንም ለማነጋገር አለመፍቀዱን ለማወቅ ተችሏል። አብዲ ሙሃመድ በፋሽስቱ ወያኔ ቱባ ሹማምንት ሽፈራ ጃርሶ የተመራውን ቡድንም እኔን ከማንም ጋር ለማደራደር ሞራሉም ሆነ አቅሙ የላችሁም፤ አትመጥኑኝም ሲል አዋርዶ መሸኘቱንም ለማወቅ ችለናል። ይህ በእንዲ እንዳለ በሹማምንቱ መካከል የተፈጠረውን ሽኩቻ ተከትሎ አገዛዙ በፌደራሊዝም ስም እየተጫዎተ ያለውን የፌዝ ቁማርን ገሃድ አውጥቶ ያሳየ እውነታ ነው ሲሉ አንዳንድ አስተያየት ሰጭዎች መናገራቸውን ለማወቅ ተችሏል። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## በውጭ አገራት እየተደረገ ያለው ህዝባዊ እምቢተኝነት ትግል ተጠናክሮ ቀጥሏል

ፋሽስቱ ወያኔ በህገወጥ መንገድ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ከየመን ሰንአ አፍኖ መውሰዱን እንዲሁም በሶማሌ ክልል በኦጋዴን አካባቢ በሶማሌ ተወላጅ ኢትዮጵያውያን ላይ ያደረሰው የንፁሃን ዜጎች ጭፍጨፋ ለመቃዎም በአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ የተሰባሰቡት ኢትዮጵያውያን በዲሲ የሚገኘውን የወያኔ ኢንባሲ ዘልቀው በመግባት በኢምባሲው ላይ የተሰቀለውን ባለ ኮከብ የወያኔ ባንድራ አውርደው በኢትዮጵያ ባንድራ ተክተውታል። አንድ የኤምባሲው ባልደረባ ኢትዮጵያውያኑን በማስፈራራት ለመመለስ ሶስት ጊዜ ጥይት በተከታታይ መተኮሱን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን የተቆጡት ኢትዮጵያውያኑ ከፊት ለፊታቸው እየተተኮሰ ለነበረው ጥይት ቁብ ባለመስጠት ወደ ፊት ገስግሰው የፈለጉት አላማ ፈጽመው መመለሳቸውን ለማወቅ ተችሏል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የጥይት ቶክሱን ተከትሎ በአከባቢው የደረሱት ፖሊሶች ኤምባሲውን ማዘጋታቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በኢትዮጵያውያኑ ላይ ጥይት ተኩሷል የተባለው ግለሰብም በቁጥጥር ስር ሊውል መቻሉ ተዘግቧል።

## አሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ ዉስጥ የሚገኘዉ  የወያኔ ኤምባሲ በኢትዮጵያዉያን ከፍተኛ ተቃዉሞ ገጠመዉ

በቅርቡ በጋምቤላ ክልል መዥንግር ዞንና በኦጋዴን የሶማሌ ተወላጅ ኢትዮጵያውያን ላይ የተፈጸመውን ህገወጥ የጅምላ ግድያ በመቃወም እንዲሁም በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ተላልፎ መሰጠትና በጠላት እጅ መውደቅ ያስቆጣቸው ነዋሪነታቸው በአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲና አካባቢዋ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ሰኞ እለት በወያኔ ኢንባሲ ላይ የወሰዱት ቁጣ የተቀላቀለበት ተቃውሞና የእምቢተኝነት እርምጃን ተከትሎ በአገዛዙ ቅጥረኛ ግለሰብ የተሰነዘረባቸው የተኩስ እሩምታ በአለማቀፍ ደረጃ አነጋጋሪ ሆኖ ቀጥሏል። የተቃውሞ እርምጃውን ተከትሎ በኢትዮጵያውያኑ ላይ የተከፈተባቸውን የተኩስ እሩምታ ከ 30 በላይ በሚሆኑ አለማቀፍ የዜና አውታሮችና ጋዜጦች በፊት ገፃቸው ይዘው በመውጣት ለአለም ህዝብ ማ ስነበባቸው ታውቋል። ከነዚህ የዜና አውታሮች ውስጥ ሮይተርስ፤ ዋሽንግተን ፖስት፤ ፎክስ ኒውስ፤ አጃንስ ፋራንስ ፍሬስ እና ሌሎቹም ሰፊ ሽፋን በመስጠት ጉዳዩን መዘገባቸውን ለማወቅ ተችሏል። ድርጊቱ የተለመደ አለመሆኑን የዘገቡት የዜና አውታሮቹ በሰላማዊ ሰልፈኞቹ ላይ የተኩስ እሩምታ የከፈተውን የጉጅሌውን ቅጥረኛ ግለሰብ እየደጋገሙ ማሳየታቸው ታውቋል። ጉዳዩ በአሜሪካ የወንጀል ምርመራ ቢሮ ተይዞ ከፍተኛ ክትትልና ምርምራ እየተደረገበት እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል።

ይህ በእንዲ እንዳለ ጉዳዩ በማስመልከት አስተያየቱን አንድ ተቀማጭነቱን አሜሪካ ላደረገ ኢትዮጵያ ፈርስት ለተባለ የአገዛዙ ደጋፊ ሬዲዮ ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## አሜሪካ በኢትዮጵያ ላይ የያዘችውን ፓሊሲ ትመርምር

መስከረም 15 ቀን 2007 ዓም፣ የዩ. ኤስ. አሜሪካ ፕሬዚዳንት ባራክ አቦማና ባልደረቦቻቸው በአንድ በኩል ኃይለማርያም ደሣለኝና አለቆቹ በሌላ በኩል ሆነው የሁለትዮሽ ስብሰባ ተደርጎ ነበር። በዚህ ስብሰባ ላይ ፕሬዚዳንት ኦባማ ያደረጉት ንግግር የዲፕሎማሲ ጨዋነት ከሚጠይቀው ርቀት በላይ ተጉዘው ሸሪኮቻቸው ባልሠሯቸው ጀብዶች ማሞገሳቸው አሳዝኖናል። ፕሬዚዳንት ኦባማ ከላይ በተጠቀሰው ቀን ያደረጉት ንግግር ላይ በርካታ ስህተቶች፣ ህፀፆችና ግድፈቶች የያዘ ከመሆኑም በላይ አንዳንዱ አስተያየት የኢትዮጵያዊያንን ክብር የሚነካ ሆኖ አግኝተነዋል።

ፕሬዚዳንቱ ንግግራቸውን የጀመሩት “ኢትዮጵያ በዓለም ከሁሉም በላይ በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ ላይ ያለች አገር ነች“ በሚል ዓረፍተ ነገር ነበር። የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ ጽ/ቤት የፈጠራ ቀመሮች በዓለም ባንክ በኩል ዞረው በሚስ ሱዛን ራይስ ተቀነባብረው በባራክ ኦባማ አንደበት መስማት የሚያሳፍር ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ኦባማ የተናገሩትን ዓረፍተ ነገር ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥና ራድዮ ደጋግሞ ሰምቶ ሰልችቶታል። ኦባማ፣ ይህ የተሰለቸ ዓረፍተ ነገር በእሳቸው አንደበት ሲነገር ስለሚሰጠው ትርጉም ጥቂት ቢያስቡ ኖሮ ለእሳቸውም ለአሜሪካም የተሻለ ነበር ብለን እናምናለን። “በአንድ ወቅት ራሷን መመገብ ያቅታት የነበረችው አገር ዛሬ ከፍተኛ እድገት የሚታይባት ሆናለች፤ አሁን የግብርና ብቻ ሳይሆን [የኤሌክትሪክ] ኃይልንም በመሸጥ በቀጠናው ቀዳሚነት ይዛለች” ሲሉ ያሞካሿት ኢትዮጵያን ኢትዮጵያዊያን የማያውቋት መሆኑን፤ እሳቸው የሚያወድሷት ኢትዮጵያ በህወሓት ፕሮፖጋንዳ እንጂ በመሬት ላይ የሌለች መሆኑን ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ማወቅ ነበረባቸው። በአንፃሩ የእውነተኛዋ ኢትዮጵያ 70% ሕዝብ በድህነት ወለል በታች በሆነ ኑሮ ሕይወቱን እየገፋ እንደሆነ፤ የሚሊዮኖች ኢትዮጵያዊያን የእለት ጉርስ ምንጭ የአሜሪካና የአውሮፓ አገሮች እርዳታ መሆኑን ፕሬዚዳንት ኦባማ አያውቁም ማለት ይከብዳል። ፕሬዚዳንት ኦባማ የተናገሩለት የመብራት ኃይልም ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተስፋ ተረት መሆኑን፤ ዛሬም የኢትዮጵያዊው የምሽት ኑሮ የሚገፋው በባትሪ፣ በሻማና በኩራዝ መሆኑን ፕሬዚዳንት ኦባማ አያውቁም ማለት ያስቸግራል።

ፕሬዚዳንት ኦባማ ከተናገሩት ውስጥ ትርጉም የሚሰጥ ነገር ቢኖር ስለ “ሰላም ማስከበር” የተናገሩት ነው። የህወሓት አገዛዝ፣ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊትን ገንዘብ ባለበት እና አሜሪካ ወደ ፈለገችው ቦታ ሁሉ የሚልክ መሆኑ ይታወቃል። ስለሆነም የጦሩ የሰላም ማስከበር ሥራ ማሞካሸታቸው የሚጠበቅ ነው። እንዲያውም የፕሬዚዳንቱ ሙሉ ንግግር የተቃኘው ከዚህ አቅጣጫ ይመስላል። እንደዚያ ባይሆን ኖሮ የራሳቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ያወጣውን የሰብዓዊ መብት አያያዝ ሪፖርትን ውድቅ የሚያደርግ ነገር ባልተናገሩም ነበር። አንዳችም ነፃ ተቋማት በሌሉበት አገር ውስጥ ፍትሃዊ ምርጫ የሚባል ነገር ሊኖር እንደማይችል አውቀው ቀዳሚው ጥያቄዓቸው የሰብዓዊ መብቶች መከበር እና የነፃ ተቋማት ግንባታ ጉዳይ ባደረጉት ነበር። ፕሬዚዳንት ኦባማ ስለኢትዮጵያ ተጨንቀው ቢሆን ኖሮ የራሳቸው ስቴት ዲፓርትመን የዘንድሮውን የሰብዓዊ መብት አያያዝ ሪፓርት ያስታውሱ ነበር። ሪፓርቱን በማስታወሳቸው ብቻ በግፍ እየታሰሩ ስላሉት ዜጎች፣ በኦጋዴን፣ በኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በአፋር እና በአማራ እየተጨፈጨፉ ስላሉ ዜጎች፣ ስለ መሬትና የሀብት ዘረፋ፣ ስለፍትህ እጦት፣ ስለ ተቋማዊ ዘረኝነት እና ሌሎችም በርካታ ጉዳዮች እንዳነሱ ይቆጠር ነበር፤ ምክንያቱም ያ ሪፓርት የያዘው ይህንን ሁሉ ነው። ፕሬዚዳንት ኦባማ ግን የንግግራቸው ግብ ዘማች ወታደር ማግኘት በመሆኑ የራሳቸውን የስቴት ዲፓርትመንት ሪፓርት ትተው የወያኔን ሪፓርት ይዘው የቀረቡ አስመስሎባቸዋል። ይህ አካሄድ አሜሪካ ወደማትፈልገው የጦር አረንቋ የሚላኩ የሠራዊት አባላት ሊያስገኝ ቢችልም የሚያስከትላቸው ጉዳቶችም መታየት ነበረባቸው። የንግግራቸው ፈጣን አሉታዊ ውጤት ለማየት ቀናትም አልፈጀም፤ እነሆ በኦባማ አይዞህ ባይነት የተነቃቁት የህወሓት ገዳዮች ከኢትዮጵያ አልፈው በአሜሪካ ምድርም በኢትዮጵያዊያን ላይ መተኮስ ጀምረዋል።

የኦባማ ንግግር ትኩረት የፀጥታ ጉዳዮች ሆኖ ኢኮኖሚ የግኑኝነት ማሳለጫ ሆኖ ቀርቧል፤ የሰብዓዊ መብት አጠባበቅና የዲሞክራሲ ጉዳዮች ደግሞ ፈጽመው ተገፍተው ወጥተዋል። ይህ ንግግር አሜሪካ በኢትዮጵያ ላይ የምትከተለውን ፓሊሲ አመላካች ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በፀጥታ ጉዳይም ቢሆን አሜሪካ የያዘችው አቋም በረዥም ጊዜ የኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን የአሜሪካን ጥቅም የሚጎዳ ነው ብሎ ያምናል። ኢትዮጵያ ለአሜሪካ ከወታደር ምንጭነት በላይ የምታገለግል አገር ናት። ኢትዮጵያ ውስጥ ከራሱ ሕዝብ ጋር የታረቀ መንግሥት መኖር ለቀጠናው ሰላም እና ብልጽግና ወሳኝ ከመሆኑም በላይ የቀጠናው ሰላምና ብልጽግና የአሜሪካም ስትራቴጂያዊ ጥቅም ነው ብለን እናምናለን። የአጫጭር ጊዜ ጊዜዓዊ ጥቅሞችን ብቻ በመመልከት አምባገነኖችን መደገፍ አሜሪካን ምን ያህል ውድ ዋጋ እያስከፈላት እንደሆነ በዓይኖቻችን እያየነው ያለ ሀቅ ነው። አሜሪካ አምባገነኖችን መደገፏን ከቀጠለች ፈጥኖም ይሁን ዘግይቶ የምታገኘው እስካሁን ስታገኝ የነበረውን ውግዘትና የጽንፈኞች መጠናከር ነው። አሜሪካ የተሳሳተ ፓሊሲ በያዘችባቸው አገሮች ሁሉ ግንባር ቀደም ተጎጂዎች ለዘብተኞችና ዲሞክራቶች ሲሆኑ እየተጠናከሩ የሚመጡት ደግሞ ጽንፈኖች ናቸው። አሁንም አሜሪካ በኢትዮጵያ ላይ የያዘችውን ፓሊሲ የአገሪቱን የዲሞክራሲ ኃይሎችን የሚያዳክም እና ጽንፈኛ ኃይሎችን የሚያበረታታ እንደሆነ ከወዲሁ ሊጠን ይገባዋል።

ዩ. ኤስ አሜሪካ የምትመራባቸው የነፃነት፣ የእኩልነትና የፍትህ እሴቶች የግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እሴቶችም ናቸው። ኢትዮጵያዊያን እንደ አሜሪካ ዜጎች ሁሉ ፍትህን፣ ነፃነትን፣ እኩልነትንና ዲሞክራሲን ይሻሉ፤ እነዚህ መሻት ደግሞ መብታቸው ነው ብሎ ግንቦት 7 ያምናል፤ ለዚህም ይታገላል። አሜሪካ ይህን ትግል ማገዝ ይገባታል። በተግባር የምናየው ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። አሜሪካ ለአጫጭር ጊዜ ጥቅም ስትል ከአምባገነን ኃይሎች ጋር ማበሯ የዓላማ ተጋሪዎቿን እያዳከመ መሆኑ የወቅቱ የዓለም ሁኔታ የሚመሰክረው ሀቅ ነው። በኢትዮጵያ ላይ እየተከተለችው ያለው ፓሊሲው ተመሳሳይ የረዥም ጊዜ መዘዝ እንዳያመጣ ያሰጋል። ይህ እንዳይሆን እርምት የሚገባው አሁን ነው።

ስለሆነም፣ ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ ዩ. ኤስ. አሜሪካ በኢትዮጵያ ላይ የያዘችውን ፓሊስ እንደገና እንድትመረምር እና ዘረኛና አምባገነኑን የህወሓት አገዛዝን መርዳት እንድታቆም አበክሮ ያሳስባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ! ! !**

---

## የአውሮፓ ህብረት የአንዳርጋቸዉ ጽጌን መታሰር አወገዘ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የአቶ አንዳርጋቸው ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ በመሆኑ በተለይ እንግሊዝ እስካሁን እያሳየችው ከነበረው በጉዳዩ ዙሪያ ከአገዛዙ ጋር የመለሳለስ አቋም እንድትወጣና ለዜጋዋ የህይወት ደህንነት ዋስትና እንድትቆም አበክረው መጠየቃቸው ታውቋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በዚሁ የኮሚሽኑ ስብሰባ ላይ የጉጅሌው ወያኔ ተወካይ የቀረበ ሲሆን አሁንም እንደወትሮው ሁሉ በውሸት የታጨቀ የማስተባበያ ሪፖርት ማቅረቡን ለማወቅ ተችሏል።

በተያያዘ ዜና የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ተላልፎ መሰጠትና በጠላቶች እጅ መውደቅ በመቃወም በውጭ አገራት እየተደረገ ያለው የተቃውሞ እንቅስቃሴ በተለይ በአሜሪካና በእንግሊዝ አገራት በተጠናከረ ሁኔታ እየተደረገ መቀጠሉ የሚታወቅ ሲሆን አሁንም ተመሳሳይ የተቃውሞ ሰልፎች በተለያዩ የአለም አገራት እየተሰናዱ መሆኑን ለሬዲዮ ክፍላችን የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

የአውሮፓዉ ኅብረት ተወካይ አቶ አንዳርጋቸው በአሁኑ ወቅት መሠረታዊ የሆኑትን ሰብዓዊ መብቶቹን ተነፍጓል፡፡ የኤምባሲ ካውንስለሮች እንዲጐበኙት አይፈቀድም፤ ቤተሰቦቹ፣ የሕግ አማካሪዎችም ሆነ ገለልተኛ የሕክምና አገልግሎትም አልተፈቀደለትም ብለዉ ከተናገሩ በኋላ በሰኔና በሐምሌ ወር አቶ አንዳርጋቸው በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ለሁለት ጊዜ መቅረባቸውን አስረድረዉ ቪዲዮዎቹ ኤዲት የተደረጉ ቢሆንም አቶ አንዳርጋቸው በጥሩ የጤንነት ሁኔታ ላይ እንዳልሆኑ ለመገመት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡ ሁለቱንም ቪዲዮዎች የእንግሊዝ የአዕምሮ ሕክምና ባለሙያዎች (ሳይካትሪስቶች) በመመልከት ግምገማ እንዳደረጉና የአቶ አንዳርጋቸው የአዕምሮ ሁኔታ እየተበላሸ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሳቸውን ተወካይዋ ገልጸዋል፡፡ <<ለእንደዚህ ዓይነት የአዕምሮ ሁኔታ መቃወስ በእስር ቤት እየተፈጸመበት ያለ ግርፋት (ቶርቸር) ሊሆን እንደሚችል ባለሙያዎቹ ገምተዋል፤>> ብለዋል፡፡ ሪፖርቱን ለኅብረቱ ንዑስ ኮሚቴ ያቀረቡት ተወካይ ከላይ የተጠቀሱት ሐሳቦች ሙሉ በሙሉ በመረጃ ላይ የተመሠረቱ እንዳልሆኑ፣ ለዚህም ምክንያቱ አቶ አንዳርጋቸውን ለማግኘት ባለመቻሉ ነው ብለዋል፡፡

አቶ አንዳርጋቸው በሌሉበት ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት የሞት ቅጣት የተወሰነባቸው በመሆኑ፣ የእንግሊዝ መንግሥትን እንዳሳሰበውና በዚህ ረገድም የኢትዮጵያ መንግሥትን ቢጠይቅም ምንም ዓይነት ማስተማመኛ አለመስጠቱን አስረድተዋል፡፡ <<በመሆኑም አቶ አንዳርጋቸው የኢትዮጵያ መንግሥት በፈጸመበት እገታና ሕግን ያልጠበቀ እስር ጉዳት እየደረሰበት ነው፤>> ብለዋል፡፡ የአውሮፓ ኅብረት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የሚለቀቁበትንና ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚቀላቀሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ተባብሮ እየሠራ ቢሆንም፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የመተባበርና የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች በመመለስ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

ሃይለ ሀሳብ

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 334 መስከረም 24 2007 ገጽ

# ሰልጣኙንም አሰልጣኙንም ያንገሸገሻቸዉ ሥልጠና

አባትና የ10ኛ ክፍል ተማሪ ልጁ አምርረዉ ሲጨቃጨቁ እናት ትደርስና . . . . እባክሽ ልጄ አባትሽ የሚልሽን ለምን አትሰሚም ብላ ልጇን ትቆጣታለች። ልጅት ከተቀመጠችበት ትነሳና ምነዉ እማዬ ምኑን ነዉ የምሰማዉ፤ አባዬኮ እሱ እራሱ የማያዉቀዉን ነገር ላሳይሽ እያለኝ ነዉ ብላ ንግግሯን ሳትጨርስ በቁጣዉ ብዛት ፊቱ እንደ ፊኛ ያበጠዉ አበቷ ካንቺ ማወቅ ዬኔ አለማወቅ ይሻላል፤ይልቅ የምልሽን ስሚ ብሎ ጮኸባት። ወጣቷ ተማሪ ወላጅ አበቷ ከስምንተኛ ክፍል በላይ ዘልቀዉ እንዳልተማሩ ብታዉቅም ለግዜዉ ማድረግ የምትችለዉ ምንም ነገር አልነበረምና እሽ አባዬ ብላ አባቷን መስማት ጀመረች፡፡ ይህ የአባትና የልጅ ስሚኝ አልሰማም ጭቅጭቅ ባለፉት ሁለት ወራት መሀይሞቹ የወያኔ ካድረዎችና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በየስልጠና አዳራሹ ያደረጉትን ፍጥጫ አስታወሰኝ። ይህ አብዛኛዉን ዕድሜያቸዉን ትምህርት በመማር በሳለፉት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና በወጉ ስምንተኛ ክፍልን ባላጠናቀቁ የወያኔ ካድሬዎች መካከል በክረምቱ ወራት ተጀምሮ አሁን ድረስ የዘለቀዉ የ"አሰለጥናለሁ አታሰለጥንም" ትንግርታዊ ድራማ ወያኔ አስካሁን ከሰራቸዉ ድራማዎች በአይነቱ ለየት ያለ ድራማ ነዉ።

የወያኔ ምርጫዎች ምንም አይነት ዉድድር የማይታይባቸዉ ማንም ተወዳደረ ማንም ወያኔ ብቻ የሚያሸንፍባቸዉና ምርጫዎቹ ከመካሄዳቸዉ በፊት የት ቦታ እነማን ማሸነፍ እንዳለበቸዉ ተወስኖ ያለቀላቸዉ የለበጣ ምርጫዎች ናቸዉ። ወያኔ ግን "ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል" እንደሚባለዉ ምርጫዉ በቀረበ ቁጥር የሚያከለፈልፍ በሽታ ይይዘዋል። ኢትዮጵያ ዉስጥ በ1997ና በ2002 ዓም የተደረጉትን ምርጫዎችና እርግጠኞች ነን አሁንም በ2007 ዓም የሚደረገዉን ምርጫ የሚለያያቸዉ ነገር ቢኖር በእያንዳንዱ ምርጫ መኸል የአምስት አመት ልዩነት መኖሩ ነዉ እንጂ የምርጫዉን ዝግጅት፤ ሂደትና ዉጤት በተመለከተ ይህ ነዉ ተብሎ ሊነገር የሚችል ልዩነት የለም። ሁሉም ምርጫዎች የሚካሄዱት ወያኔ የምርጫ ተቋሞች፤ ሜድያዉንና ፍርድ ቤቶችን ሙሉ በሙሉ በሚቆጣጠርበት ሁኔታ ዉስጥ ነዉ። በዚህ ላይ ቅድመ ምርጫዎችን የሚቆጣጠረዉ፤ በምርጫዉ ብቸኛ ተወዳዳሪ የሆነዉና ህዝብ የሰጠዉን ድምጽ የሚቆጥረዉ ወያኔ እራሱ ነዉ። ይህም ሁሉ ሆኖ ወያኔ ከሱ ዉጭ ማንም ምርጫዉን እንደማያሸንፍ በልቡ እያወቀ አምስት አመት እየቆጠረ የሚመጣዉ ምርጫ በቀረበ ቁጥር ግርግር መፍጠር ይወዳል። በ1997 በተደረገዉ ምርጫ ማንም አያሸንፈኝም ብሎ ሜድያዉንና የፖለቲካ ምህዳሩን ትንሽም ቢሆን ለቀቅ አድርጎ የነበረዉ ወያኔ በ2002 ዓም ይጋፉኛል ብሎ የጠረጠራቸዉን ሁሉ ማሰር፤ መደብደብና እንቅስቃሴያቸዉን መግታት ጀመረ። አሁን በ2007 ዓም ደግሞ ገና በግንቦት ወር ለሚካሄደዉ ምርጫ የኢትዮጵያን ወጣት ካልተቆጣጠርኩ በሚል ትልቅ ዘመቻ ጀምሮ በከፍተኛ በሁለተኛ ደረጃና ዩኒቨርሲቲ ዉስጥ የሚገኙትን የአገሪቱ ወጣቶች በሥልጠና ሰበብ ወያኔያዊ የፖለቲካ ጠበል እያጠመቃቸዉ ነዉ።

ብዙ ኢትዮጵያዊያን ወያኔን ዘረኛ ነዉ፤ ጎጠኛ ነዉ፤ ነብሰ ገዳይ ነዉ ይሉታል። አዎ እነዚህ ሁሉ የወያኔን ማንነትና ምንነት በትክክል የሚያሳዩ ቃላት ናቸዉ። ወያኔ ግን ከእነዚህ ዉጭ ሌሎች ብዙ መገለጫዎች አሉት፤ ለምሳሌ ወያኔ መዋሻት የማይሰለቸዉ ዉሸታም ነዉ፤ ዕኩይ ነዉ፤ ጨካኝና የለየለት ሙብት ረጋጭም ነዉ። እነዚህ የወያኔ ባህሪያት ሁሉ ያናድዱናል ወይም ያስቆጡናል እንጂ አይገርሙንም ወይም እየኮረኮሩ አያስቁንም። ጉደኛዉ ወያኔ የሚገርሙና የሚያስቁ ባህሪያትም አሉት። ወያኔ የቁጥር ጨዋታ ይወዳል፤ በተለይ ከቁጥርና ከቁጥርም በዛ ካለ ቁጥር ጋር ለየት ያለ ፍቅር አለዉ። ለምሳሌ የኢትዮጵያ የአገር ዉስጥ ምርት ከዉጭም ከዉስጥም ተገፍቶ 5% ከጨመረ ወያኔ የሚነግረን 10% አደገ ብሎ ነዉ። ኢትዮጵያ ዉስጥ የትምህርት ጥራት ተንኮታኩቶ ከመዉደቁ የተነሳ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀዉ ወደ ስራ አለም በሚገቡ ተማሪዎችና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸዉን ጨርሰዉ ኮሌጅ በሚገቡ ተማሪዎች መካከል ያለዉ ልዩነት ትንሽ ነዉ፤ ወያኔ ግን በኔ ዘመነ መንግስት የዩኒቨርሲቲዉ ብዛት ብቻ ሳይሆን ከዩኒቨርሲቲ የሚመረቁ ተማሪዎች ብዛት ከ300% በላይ አደገ እያለ ይፏልላል። ካለፈዉ ሐምሌ ወር ጀምሮ ያለፍላጎታቸዉና ያለፈቃዳቸዉ በግድ ወደ ሥልጠና ማዕከላት እየገቡ የወያኔን ርካሽ ፕሮፓጋንዳ እንዲጋቱ የሚገደዱ ወጣቶችም ጉዳይ ይህንኑ ወያኔ ከቁጥርና ከብዛት ጋር የተጠናወተዉን ፍቅር የሚያሳይ ነዉ። ይህ ወያኔ በየክልሉ ሥልጠና ብሎ የጀመረዉ ቧልት የሰልጣኞቹን እዉቀት የሚያዳብር አይደለም ወይም ለአገራችን ለኢትዮጵያም በምንም መልኩ የሚጠቅም አይደለም። የሥልጠናዉ ብቸኛ አላማና ጥቅም በወጣቱ ላይ ተፅዕኖ በማሳደር የወያኔን አባላት ማብዛት ነዉ። ወያኔ ድርጅታዊ የፓርቲ ስራዎችን የሚሰራዉ መንግስታዊ ተቋሞችን በመጠቀም ከመንግስት ካዝና በሚወጣ ገንዘብ ነዉና እሱን የሚያስደስተዉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አባላት አሉት ተብሎ መነገሩ ነዉ እንጂ እነዚህ አባላት ታማኝ ይሁኑ አይሁኑ ወይም ድርጅታዊ ስራ ይስሩ አይስሩ ለወያኔ ጉዳዩ አይደለም።

ወያኔ በዕረፍት ላይ የሚገኙ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ከያሉበት በግድ አስመጥቶ ሥልጠና እንዲወስዱ ለማድረግ የወሰዳቸዉ እርምጃዎች ሁሉ በወያኔና በተማሪዎቹ መካከል ያለዉን ሰፊ የፖለቲካ ልዩነት አጉልቶ ከማዉጣቱ ባሻገር ይህ ሳይጀመር የከሸፈዉ ስልጠና ለወያኔ ምንም የፈየደዉ ፋይዳ የለም። እንዳዉም አብዛኛዉ ተማሪ የወያኔ መሪዎችን አንገት የሚያስደፉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሥልጠና የሚያስፈልገዉ ለተማሪዎቹ ሳይሆን ለራሳቸዉ ለአሰልጣኝ ነን ባዮቹ መሆኑን በተግባር አሳይቷል። በብዙዎቹ የስልጠና አዳራሾች የወያኔ ካድሬዎች ተማሪዎቹ የሚጠይቁትን ጥያቄ መመለስ አለመቻላቸዉ ብቻ ሳይሆን ካድሬዎቹ በሚጠየቁት ጥያቄ እየተበሳጩ ጥርሳቸዉን ሲነክሱ ታይተዋል። በእርግጥም ጎንደር ዉስጥ የነበረዉን ጄኔሬተር ነቅላችሁ ዬት አደረሳችሁት ከሚል አፋጣጭ ጥያቄ ጀምሮ አንዳርጋቸዉ ጽጌን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን በጠየቁ ተማሪዎች ላይ አሰልጣኝ ካድሬዎች "ከእናንተ ጋር በኋላ እንገናኛለን" እያሉ ሲዝቱ ተደምጠዋል።

ኢትዮጵያ ትናንትም ዛሬም ካለ ለጋሽ አገሮች ዕርዳታ መንፈቅ መዝለቅ የማትችል ደሃ አገር ናት፤ ሆኖም የወያኔ መሪዎችና ቤተሰቦቻቸዉ የሚዘርፉትን ገንዘብና አላግባብ የሚያባክኑትን የአገር ሃብት የተመለከተ ማንም ሰዉ ድርጊታቸዉ ከደሃዋ አገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በፍጹም እንደማይገናኝ ለመገንዘብ ግዜ አይፈጅበትም። ወያኔ ገነባሁ ብሎ የሚያፈርሳቸዉንና በየስብሰባዉና በየጉባኤዉ ከሚያባክነዉ ግዙፍ የአገር ኃብት ዉጭ ከሰሞኑ ምንም አገራዊ ጥቅም በሌለዉና ሠልጣኞቹ አንፈልግም ብለዉ ለተዉት ሥልጠና የሚያባክነዉ የህዝብና የአገር ገንዘብ እጅግ በጣም ብዙ ነዉ። ለምሳሌ ለአሰልጣኝ ካድሬዎች ከሚወጣዉ የትርንፖርትና የዉሎ አበል ዉጭ ለእያንዳንዱ ሰልጣኝ ተማሪ በቀን የሚከፈለዉ ሃምሳ ብር ቁጥራቸዉ ከ600 ሺ በላይ በሆኑ ሰልጣኝ ተማሪዎች ልክ ሲሰላ እጅግ በጣም ብዙ ገንዘብ ነዉ።

ለመሆኑ ዜጎች የሚላስና የሚቀመስ አጥተዉ በሚራቡበት አገር፤ ወጣቶች ስራ ፍለጋ ያደጉበትን መንደር ጥለዉ ባሕር እየተሻገሩ በሚሰደዱበት አገርና የገንብዘብ እጥረት እየተባለ ብዙ ፕሮጀክቶች በሚታጠፉበት አገር ወያኔ ከየት እያመጣ ነዉ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ እየከፈለ ምንም እርባና የሌለዉ የፖለቲካ ሥልጠና ሥልጠናዉ በፍጹም ለማያስፈልገዉ የህብረተሰብ ክፍል የሚሰጠዉ? ደግሞስ ከዉጭ አገር ምንጮች ምንም አይነት የገንዝብ እርዳታ እንዳያገኙ በህግ የተከለከሉ የፖለቲካ ድርጅቶች የስራ ማስኬጃ ወጪያቸዉን መሸፈን አቅቷቸዉ በሚንገዳገዱበት አገር ምን ቢደረግ ነዉ ወያኔ የራሱን ፓርቲ ስራዎች በመንግስትና በህዝብ ገንዘብ የሚያሰራዉ?

የወያኔና የገንዝብ ጉዳይ ከተነሳ እነዚህ ጉደኞች ቢነገር ቢነገር የማያልቅ ከገንዘብ ጋር የተቆራኘ ብዙ የቆሸሸ ታረክ አላቸዉ። ከሰሞኑ ኢትዮጵያ ዉስጥ የአገሪቱን የአየር ሞገዶች ከዳር እስከ ዳር ያጨናነቀዉ ከዚሁ ከወያኔ የረጂም ግዜ ቆሻሻ ታሪክ ጋር የተያያዘዉ የገንዘብ ጉዳይ ነዉ። ከሰሞኑ የኢትዮጵያን ባንኮች፤ ትላልቅ መደብሮችና ዘመናዊ የመገበያያ አዳራሾች በብዙ መቶ ሚሊዮኖች በሚቆጠር ሀሰተኛ ገንዘብ ተጨናንቀዋል። ይህ ማን፤ መቼ፤ ከየትና እንዴት እንዳሰራጨዉ የማይታወቅ የሀሰተኛ ገንዝብ ዝርጭት ኢትዮጵያ ዉስጥ እያንዳንዱን ሰዉ እያነጋገረ ነዉ። የወያኔ ፖሊሶች ከየባንኩና ከየገበያ አዳራሹ በየቀኑ ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ ሀሰተኛ የብር ኖቶች እየሰበሰቡ መሆናቸዉን ቢናገሩም ከዚህ ሀሰተና ገንዘብ ስርጭት በስተጀርባ የማን እጅ እንዳለበት ግን ምንም የተነፈሱት ነገር የለም። እንደዚህ ብዛት ያለዉ ሀሰተኛ የገንዘብ ኖት ደግሞ አቅምና እዉቀት በሌላቸዉ ተራ ወንጀለኞች የሚሞከር ወንጀል አይደለም። ለዚህም ይመስላል ብዙ ኢትዮጵያዉያን በዚህ ሀሰተኛ ገንዘብ ስርጭት ዉስጥ ያለምንም ጥርጥር የወያኔ ባለስልጣኖች እጅ አለበት ብለዉ በድፍረት አፋቸዉን ሞልተዉ የሚናገሩት። መቼም መሬት ቆፍሮ ቦምብ እየቀበረ በተቃዋሚዎች የሚያሳብበዉና በፈንጂ ህዝባዊ ተቋሞችን እያፈረሰ ሽብርተኛ ብሎ በፈረጃቸዉ ድርጅቶች ላይ ጣቱን የሚቀስረዉ ወያኔ የደረሰበትን ከፍተኛ የገንዘብ ጉድለት ለመሙላት ሀሰተኛ ገንዘብ አሰራጭቶ ሊያጠፋቸዉ በሚፈልጋቸዉ ሰዎችና ቡድኖች ላይ አያመካኝም ማለት አይቻልም። ለሁሉም የወያኔ ነገር አንቺዉ ታመጪዉ አንቺዉ ታሮጪዉ ነዉና ይህ የሀሰተኛ ገንዘብ ስርጭት የራሱ የወያኔ ስራ እንደሆነ ከራሱ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች የምንሰማበት ግዜ ሩቅ አይደለም። በነገራችን ላይ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዉያንን የሙጥኝ ብሎ ተጣብቆ የሚያሰቃያቸዉ የዋጋ ንረት መሠረታዊ መንስኤዉ መለስ ዜናዊ በህይወት ከነበረበት ግዜ ጀምሮ ከአገሪቱ የማምረት አቅም በላይ በሆነ መልኩ በገፍ እየታተመ ወደ ኤኮኖሚዉ ዉስጥ እንዲገባ የተደረገዉ የገንዘብ አቅርቦት ነዉ። ይህ ዘንድሮ ስሙን ቀይሮ "ሀሰተኛ የገንዝብ ስርጭት" ተብሎ አገራችንን የሚያምሳት በሽታም የዚሁ የተለመደ ወያኔ እያተመ የሚያሰራጨዉ የገንዘብ አቅርቦት ችግር አካል ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለዉም። አለዚያማ ወያኔ በነጋ በጠባ ሚሊዮንና ቢሊዮን እያለ የሚያባክነዉ ገንዘብ ከዬት ይመጣል?

ስልጠና በየትኛዉም ማህበረሰብ ዉስጥ የእዉቀትና የልምድ ልዉዉጥ ለማድረግ የሚረዳ ጠቃሚ ተግባር ነዉ፤ ሆኖም ስልጠና ሲባል አላማ፤ አትኩረትና ግብ ኖሮት በተወሰነ ቡድን ወይም ቡድኖች ላይ የሚያነጣጥር የእዉቀትና ልምድ መቀባበያ መሳሪያ ነዉ እንጂ እንዳዉ በጅምላ የአንድ አገር ህዝብ እንዳለ ተመሳሳይ ስልጠና ይዉሰድ እየተባለ የሚደገስ የጨረባ ተዝካር አይደለም። ደግሞም ስልጠና አሰልጣኝና ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ መምህራንን ከስራ ገበታቸው በማፈናቀል ስራ ላይ መጠመዱ ታወቀ

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ከሰሞኑ ለመምህራን በሰጠው አስገዳጅ የፖለቲካ ስልጠና ከፍተኛ ቁጣና ተቃውሞ ማስተናገዱን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን አገዛዙ በአዲስ አበባ በተለያዩ ክፍለ ከተማዎች በመምህርነት ሙያ እያገለገሉ የሚገኙ ወጣት መምህራንን የፖለቲካ ስልጠናው በተሳካ ሁኔታ እንዳይካሄድ እንቅፋት ሆናችኋል፤ እንዲሁም በትምህርት ቤቶች ውስጥ ድብቅ አጀንዳ ይዛችሁ ስትንቀሳቀሱ ተገኝታችኋል በሚል መሰረት የለሽ ውንጀላ አገዛዙ ከ 15 በላይ መምህራንን ከሚሰሩበት የትምህርት ተቋም ያለፍላጎታቸው ህገወጥ በሆነ መንገድ በማስነሳት ወደ ገጠራማ ስፍራዎች እንዲመደቡ መደረጉን ለማወቅ ተችሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የያዝነው አዲሱ የስራ አመት ለመምህራን እጅግ ፈታኝ የስራ ዘመን ሊሆን እንደሚችል በስፋት እየተነገረ እንደሚገኝ የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን አመልክቷል። እንደ ዘጋቢያችን መረጃ አገዛዙ በመላ አገሪቱ ባካሄደው አስገዳጅ የፖለቲካ ስልጠናዎች ላይ በመምህራኑ ዘንድ የተጠናከረ ተቃውሞ ማስተናገዱን ተከትሎ አገዛዙ መምህራኑን ከተለያዩ ሃይሎች በህቡዕ ትሰራላችሁ የሚል መሰረተ ቢስ ክስ እየከሰሳቸው እንደሚገኝ ታውቋል። ይህንን መሰረተ ቢስ ፍረጃ ተከትሎ መምህራን በጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ ወከባ ሊፈጸምባቸው እንደሚችል ተመልክቷል። ከዚህ ቀደም በ 2004 ዓ.ም የደመወዝ ጭማሪን ተከትሎ በመላ አገሪቱ በተቀሰቀሰው የመምህራን ተቃውሞ በርካታ መምህራን ከስራ ገበታቸው መባረራቸውንና ጥቂቶቹ ደግሞ በህገወጥ መንገድ ራቅ ወዳለ ገጠራማ ስፍራዎች መመደባቸው ይታወሳል።

## ጀኔራል አበባው ታደሰ መከላከያን ለቀቁ

ወያኔ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ስር ባደረገዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ዉስጥ ትግርኛ የማይናገሩ ወይም ብቸኛዉ የአማራ ተወላጅ ባለ ከፍተኛ ማዕረግ ወታደራዊ የበላይ አዛዥ የነበሩት ጀኔራል አበባዉ ታደሰ የአዛዕነት ቦታቸዉን ለህወሓት መኮንኖች ትተዉ መከላከያ ሰራዊቱን መሰናበታቸዉ ተሰማ። እኚህ 98 በመቶ የሚሆነውን የመከላከያ ሰራዊት ከፍተኛ የአዛዥነት ቦታዎችን ከተቆጣጠሩት የህወሃት ጀኔራሎች ጎን ለጎን ከፍተኛ ወታደራዊ ስልጣን የያዙት ቦታ ጀኔራል መከላከያን የተሰናበቱት በጀ/ል ሳሞራ የኑስ ትእዛዝ ከሃላፊነታቸው ወርደዉ ዝቅ ብለው እንዲሰሩ ከተወሰነባቸው በኋላ እንደሆነ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች ገልጸዋል።

ጀ/ል አበባው ከጀ/ል ሞላ ሃ/ማርያም እና ከጀ/ል ሰአረ መኮንን ጋር በመነጋገር ጀ/ል ሳሞራ የኑስ በመከላከያ ውስጥ የሚታየውን ሙስና አልተቆጣጠሩም በሚል ሊገመግሙዋቸው ነበር የሚል ሪፖርት ቀርቦባቸው ከሃላፊነት ዝቅ እንዲሉ መደረጉን የኢትዮጵያ ሳቴላይት ቴሌቪዥን ባለፈዉ ዐመት መዘገቡ የሚታወስ ነዉ።፡፡ አመት ኢሳት በጊዜው እንደተዘገበው ጀ/ል ሳሞራ የኑስን የሚተካው ኢታማዦር ሹም ከህወሃት እጅ እንዳይወጣ ለማድረግ ተፎካካሪ ሆነው ይቀርባሉ ተብሎ የተገመቱትን ጀ/ል አበባውን ጠልፎ ለመጣል ሁለቱ ጀኔራሎች የቤት ስራውን ወስደው ሲሰሩ ቆይተዋል፡፤ ጀ/ል አበባው ግሳጼ ደርሶባቸው ከሃላፊነት እንዲለቁ ሲደርግ የህወሃቶቹ ጀ/ል ሰአረ መኮንንና ጀ/ል ሞላ ሃ/ማርያም ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው ከፍተኛ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል። በአንጻሩ ጀ/ል አበባው ከሃላፊነት ተቀንሰው ያለፉትን 9 ወራት ንብረቶቻቸውን በመሸጥ ውጭ የሚወጡበትን አጋጣሚ ሲያፈላልጉ ከርመዋል።

ጀ/ል አበባው በባህርዳር ከተማ የሚገኘውን አልዋቅ ሆቴልና ሌሎች ድርጅቶቻቸውን ለሼክ ሙሃመድ አላሙዲን ከሸጡ በሁዋላ ከአገር ለመውጣት ቢያስቡም መከልከላቸውንና የቁም እስረኛ መሆናቸውን ምንጮች ገልጸዋል። የጀ/ል አበባው የቁም እስረኛ መሆን በብአዴንና በህወሃት የመከላከያ የሰራዊት አባላት መካከል ያለውን ሽኩቻ ሊያባብሰው ይችላል የሚሉት ምንጮች፤ አንዳንድ ምልክቶች መታየታቸውን ተከትሎ በመካከለኛ ደረጃ ላይ በሚገኙ የአማራ ተወላጅ መኮንኖች ለይ ጥበቃ እና ክትትሉ ጨምሯል። የብአዴን አባል የሆኑ መኮንኖች በሰራዊቱ ውስጥ የሚታየውን የህወሃት ፍጹም የባላይነት በተደጋጋሚ ይቃወማሉ።

## አሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ ዉስጥ የሚገኘዉ የወያኔ ኤምባሲ . . .

( ከገጽ 1 የዞረ )

የሰጠው የጉጅሌው ቱባ ሹም ግርማ ብሩ በኤምባሲው ላይ ሁከት የፈጠሩት የኢትዮጵያን ዕድገት የማይፈልጉ ጥቂት ግለሰቦች ናቸው በማለት ነፃነትና ፍትህ የጠየቁ፤ እንዲሁም ህገወጥ ግድያንና እስርን ያወገዙ ኢትዮጵያውያን ላይ የተለመደ ውንጀላውን መሰንዘሩ ታውቋል። ጉዳዩን ከአሜሪካኖች ጋር በቅርበት ዲፕሎማሲያዊ በሆነ መንገድ እየተነጋገሩበት እንደሆነ የተናገረው ግርማ ብሩ ሰልፈኞቹ ተቃዉሞ እንዲያሰሙ ስለአደረጋቸው፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚደረገው ዜንችን የማሸበር፣ የመግደልና፤ የማሰር፤ እንዲሁም መረንን ስለቀቀው የሰብአዊ መብት ረገጣ ጉዳይ አስተያየት ከመስጠት ተቆጥቧል።

በአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ በኢትዮጵያውያን የተደረገው በአይነቱ ልዩ የሆነው የተቃውሞ እንቅስቃሴና በአገዛዙ ላይ ከፍተኛ ድንጋጤን ፈጥሮ እንደሚገኝም ከውስጥ ምንጫችን የተላከልን መረጃ ያመለክታል። በተለይ የህወሃት ቱባ ሹማምንት ተመሳሳይ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች በሌሎችም የአለም አገራት በሚገኙ የኢንባሲና ቆንጽላ ጽ/ቤቶች ላይ ሊደረጉ ይችላሉ በሚል ጭንቀት ውስጥ መግባታቸውንና ጉዳዩን አስመልክቶ በዝግ ስብሰባ በመምከር ላይ መሆናቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው ኢንባሲያቸው ላይ የጎለቱትን ቅጥረኛ አምባሳደር ተብየ ግርማ ብሩ በጉዳዩ ዙሪያ ለማነጋገር አስቸኳይ ጥሪ ለማድረግ በዝግጅት ላይ መሆናቸው ታውቋል።

የተቃውሞ ሰልፉ በአገር ቤት እንዲሁም በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ከፍተኛ ድጋፍ እየተቸረው እንደሚገኝም ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ይህ አይነቱ መራር ተቃውሞና እምቢተኝነት ከዚህ በበለጠ በተጠናከረ ሁኔታ መካሄድ እንዳለበት አስተያየት ሰጭዎቹ አመልክተዋል። በተለያዩ የሶሻል ሚዲያዎች ለመመልከት እንደተቻለው ኢትዮጵያውያን በሰልፉ ለነበሩት ወገኖቻቸው ያላቸውን ከፍተኛ አድናቆትና ክብር እየገለጹ እንደሚገኙ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ በርካታ ኢትዮጵያውያን ሰልፈኞቹ በኤምባሲ ላይ የወያኔን ሰንደቅ አላማ በማውረድ የሰቀሉትን ትክክለኛውን የኢትዮጵያ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ሰንደቅ አላማ የሚያሳየዉን ፎቶ በፕሮፋይል ፒክቸርነት እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ ታውቋል። በርካታ በዉጭ አገራት ያሉ የተቃዋሚ መሪዎች እና አክቲቪስቶችም በበዋሽንግተን ዲሲ በወያኔው ኤምባሲ በኢትዮጵያውያን የተካሄደውን መራር ተቃውሞ በማድነቅ የተቃውሞ እንቅስቃሴው በተጠናከረ መልኩ በሌሎችም የአለም አገራት በሚገኙ የአገዛዙ ኢንባሲና ቆንጽላ ጽ/ቤቶች ላይ መደረግ መቀጠል እንዳለበት ተናግረዋል።

በተያያዘ ዜና በስዊድን ስቶኮልምም ተመሳሳይ የተቃውሞ ሰልፍ በወያኔው ኢንባሲ ላይ ባሳለፍነው ሰኞ መደረጉንና ኢንባሲውን ለተወሰኑ ሰአታት ኢትዮጵያውያን ተቆጣጥረውት እንደዋሉ ለማወቅ ተችሏል። ኢትዮጵያውያኑ በቀጣ ወደ ኢንባሲው ዘልቀው በመግባት አገዛዙ በኢትዮጵያውያን ላይ የወሰደውንና አሁንም እየወሰደ ያለውን ህገወጥ ግድያና እስር ማውገዛቸው ታውቋል።

በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከሰሞኑ የፋሽስቱ ወያኔ ቢጋምቤላና በኦጋዴን አካባቢ የፈፀማቸውን የጅምላ ግድያዎች ለማውገዝ የተቃውሞ ሰልፎች ሊደረጉ ዝግጅቶች መጠናቀቃቸውን ለሬዲዮ ክፍላችን የደረሰው መረጃ ያመለክታል። በተቃውሞ ሰልፎቹ ላይ ኢትዮጵያውያን በአገዛዙ ላይ ያላቸውን ቁጣና እምቢተኝነት ከዚህ ቀደም ሲገልጹበት ከነበረው ሁኔታ በተለዩ መልኩ ድምጻቸውን እንደሚያሰሙ ተገልጿል።

በእንዲህ እንዳለ አንድ ሰለሞን ገ/ሥላሴ ወይም በበረሃ ስሙ ወዲ ወይኒ የተባለዉና የኤምባሲዉ የጸጥታ ሹም እንደሆነ የሚነገርለት ወንጀለኛ ግለሰብ አዲስ አበባ ያለ መስሎት ሠላማዊ ሠልፈኞቹ ላይ አከታትሎ ጥይት በመተኮሱ በፖሊሶች ቁጥጥር ስር ከዋለ በኋላ በ48 ሰዐት ዉስጥ አሜሪካንን ለቆ እንዲወጣ በታዘዘዉ መሠረት በላፈዉ ረቡዕ አዲስ አበባ መግባቱን ከምንጮቻችን የተገኘዉ መረጃ ያስረዳል። የህ የበረሃ ጭንቅላቱን ይዞ ዋሺንግተን ዲሲ ድረስ የዘለቀው ብዙዎች የ"ባህር ማዶ አግአዚ" የሚል ስም የሰጡት ግለሰብ በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ ጥይት የመተኮሱ ዜና የኢትዮጵያው-ያንንና አለማቀፍ የመገናኛ ብዙሃንን ትኩረት ስቧል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ አዲሱን ዓመት አስመልክቶ . . . ( ከገጽ 4 የዞረ )

## የአውሮፓ ህብረት የአንዳርጋቸዉ ጽጌን መታሰር አወገዘ

. . . ( ከገጽ 2 የዞረ )

ረገድ ቸልተኛ ሆኗል ሲሉ ተችተዋል፡፡

በዚህ የኅብረቱ የሰብዓዊ መብት ንዑስ ኮሚቴ ጉባዔ ላይ በ1997 ዓ.ም. የአውሮፓ ኅብረት የኢትዮጵያ ምርጫ ታዛቢ ቡድን መሪ የነበሩት አና ጐሜዝ ተገኝተው፣ በከፍተኛ ተቃውሞ የኢትዮጵያ መንግሥትን የሰብዓዊ መብት አያያዝ ሲወቅሱ፣ እንዲሁም የአውሮፓ ኅብረት አባል አገሮች እንግሊዝን ጨምሮ በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ አያያዝ ላይ ቸልተኞች ናቸው ሲሉ በምሬት ሲናገሩ ተስተውለዋል፡፡

ኅብረቱ በጉባዔው ላይ በብራሰልስ የወያኔ ኤምባሲ ዲፕሎማቶችን በጋበዘው መሠረት አንድ ዲፕሎማት ተገኝቶ ምላሽ ሰጥቷል፡ በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የዜጐች ሰብዓዊ መብት የተረጋገጠ መሆኑን በጠቅላላው የተናገረዉ የሄዉ የወያኔ ድፕሎማት አቶ አንዳርጋቸው የኢትዮጵያን ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ለማፍረስና መንግሥትን ለመገርሰስ እየተንቀሳቀሱ መሆኑን በግልጽ ያወጁና ለተመለመሉ ቡድኖች በኤርትራ ወታደራዊ ሥልጠና እየሰጡ እንደሚገኙ ተናገሯል፡፡

<<አቶ አንዳርጋቸው የሚመራው ግንቦት 7 በኢትዮጵያም ሆነ በውጭ የሚገኙ የኢትዮጵያ መንግሥት ተቋማትን እንደሚያጠቃ በቅርቡ ገልጿል፡፡ አቶ አንዳርጋቸው የእንግሊዝ ዜግነት ቢኖረውም የኢትዮጵያን መንግሥት ለመናድና መንግሥትን ለማውረድ ወታደሮችን በኤርትራ እያሠለጠነ ነው፤>> ብለዋል፡፡ <<በመሆኑም ይህ ግለሰብ ወደ ኤርትራ ለመግባት የመን ላይ ትራንዚት ሲያደርግ ኢትዮጵያና የመን ባላቸው ስምምነት መሠረት በድኅንነት ሠራተኞች ተይዞ በዕለቱ ለኢትዮጵያ ተላልፎ ተሰጥቷል፡፡ ስለዚህ ምንም የተፈጸመ የሕግ ጥሰት የለም፤>> በማለት ያገጠጠ ህገ ወጥ ድርጊቱን ከህግ ዉጭ የጠተሰራ ምንም ስራ የለም ሲል አንደተለመደዉ ሽምጥጥ አድርጎ ክዷል።

## ወያኔ የክልሉ ፕሬዚዳንት አድርጎ የሾመዉ አብዲ ሙሃመድ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ፋሽስቱ ወያኔ በፌደራሊዝም ስም ክልሎች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ስልጣን አላቸው፤ የየ ክልሎች ቱባ ሹማምንትም ጭምር ክልሎቻቸውን በነፃነት የመምራት ሙሉ ስልጣን ተጎናጽፈዋል የሚል ዲስኩር ቢነዛም አሁንም ያለው እውነታና የፈጠጠው ሃቅ ግን በተቃራኒው አገሪቱ በህወሃትና ቱባ ሹማምንቶች የከሰረና የሾረ ፖለቲካ እየታመሰች እንደምትገኝ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ የእያንዳንዱ ክልልም ሆነ የየክልሎቹ ቱባ ሹማምንት ከህወሃትና ከቱባ ሹማምንቶቹ ውጭ አዛዥም ሆነ አለቃ እንደሌላቸው በተደጋጋሚ ሲናገሩ እንደሚደመጡ በተለያየ ጊዜያት መዘገቡ ይታወሳል።

## ሰልጣኙንም አሰልጣኙንም ያንገሸገሻቸዉ ሥልጠና

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ሰልጣኝ ተግባብተዉና ሁለቱም ሚናቸዉን ወድደዉና ፈቅደዉ የሚካሄድ የጋራ እንቅስቃሴ ነዉ እንጂ ሠልጣኝ አልሰልጥንም ካለና አሰልጣኝ ደግሞ ጥያቄ የጠየቀዉን ሁሉ “ቆይ ጠብቀኝ” እያለ የሚዝትበት ከሆነ ነገሩ ሥልጠና መሆኑ ቀርቶ ጦርነት ይሆናል። ለመሆኑ ወያኔ የአገሪቱን ወጣቶች ሥልጠና ብሎ ሰብስቦ ምንድነዉ የሚላቸዉ? መልሱ ቀላል ነዉ። ከብዙዎቹ ሰልጣኞች አንደበት በግልጽ እንደሰማነዉ፤ የወያኔ ካድሬዎች በየስልጠናዉ አዳራሽ የሚናገሩት በሚቀጥለዉ ምርጫ ኢህአዴግን ካልመረጣችሁ የወደፊት ዕድላችሁ ይጨልማል፤ ከሐይማኖት አክራሪዎች እራሳችሁን አጽዱ ወይም ከሽብርተኛ ድርጅቶች ጋር እንዳትተባበሩ እያሉ ነዉ። ወያኔ በስልጣን ላይ በቆየባቸዉ አመታት ህይወቱ እንደ ሐምሌ ጨለማ የጨለመበት የኢትዮጵያ ወጣት ግን በየስልጠና አዳራሹ በተደጋጋሚ የሚጠይቀዉ እነሱ ሽብርተኛ ብለዉ ያሰሯቸዉን ጋዜጠኞችና የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ባስቸኳይ እንዲፈቱና ወያኔዎችን እራሳቸዉን በሐይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አትግቡ እያለ ነዉ።

ባለፈዉ የአዲስ አመት ዋዜማ ምሽት የግንቦት 7 የፍትህ፤ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሊ/መንበር ለኢትዮጵያ ወጣቶች ኑና ለነጻነት፤ ለፍትህና ለእኩልነት አብረን እንታገል የሚል አገራዊ ጥሪ አድረገዋል። በየዘመኑ ለወገኖቹ መብትና ነጻነት መከበር ሸንጡን ገትሮ የታገለዉ የኢትዮጵያ ወጣት የነጻነት መሪዉ ያቀረበለትን የፍትህና የእኩልነት ትግል ጥሪ ረግጦ ከወያኔ ጋር በተላላኪነት ከሚያስተሳስረዉ ሥልጠና ጋር በፍጹም እንደማይተባበር ሁላችንም እርግጠኞች ነን። ዛሬ ዕድሜዉ ከ35 አመት በታች የሆነ ኢትዮጵያዊ ወጣት አብዛኛዉን ዕድሜዉን በወያኔ ስርዐት ዉስጥ የኖረ ወጣት ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ የዚህ ዘመን የኢትዮጵያ ወጣት ወንድሙ፤ ዘመዱ ወይም የቅርብ ጓደኛዉ በወያኔ ነብሰ ገዳዮች ሲገደሉ በአይኑ እየተመለከተ ያደገ ወጣት ነዉ። ይህ ወጣት የወያኔ በደልና ግፍ የሚነገረዉ ወጣት ሳይሆን ይህንን በደልና ግፍ ለማቆም ቆርጦ የተነሳ ወጣት ነዉ። ይህ ወጣት ወያኔ ሥልጠና እያለ የሚፈጥርለትን አጋጣሚ ሁሉ እየተጠቀመ እራሱንና ወገኖቹን ነጻ ያወጣል እንጂ በሥልጠና ስም ከወያኔ በሚመጣለት ኮቶቶ እጅና እግሩን አስሮ የወያኔ ባሪያ ሆኖ አይኖርም። ለዚህ ቆራጥና አርቆ አስተዋይ ለሆነ ወጣት ያለን መልዕክት አይዞህ፤ በርታ፤ ጽና በድል የምንገናኝበትና የአገራችን ባለቤት የምንሆንበት ቀን ቅርብ ነዉ የሚል ወገናዊ መልዕክት ነዉ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!**